# 2021-2022 የወላጅ እና የቤተሰብ ተሳትፎ
# የ MCPS ታይትል I ~ የዲስትሪክት ደረጃ ዕቅድ

ይህ ዓመታዊ Title I የወላጅ እና የቤተሰብ ተሳትፎ ዕቅድ በ Title I ድረ-ገጽ ላይ ተለጥፎ በፎል ወቅት ለቤተሰቦች ተሰራጭቷል።




ጋዜጦች፣ ጥሪዎች፣ በራሪ የወረቀት ማስታወቂያዎች የመሳሰሉት የመገናኛ ህትመቶች

በ MCPS 'ዋና' ቋንቋዎች ይገኛሉ።

## ሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ

## Montgomery County Public Schools
## Title I ፕሮግራም

### የእኛ እምነት

- ★ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ታይትል I ትምህርት ቤቶች እና ቤተሰቦች በጋራ አብረው ሲሰሩ፣ ልጆች ስኬታማ ይሆናሉ ብሎ ያምናል።
- ★ MCPS የሁሉንም ቤተሰቦች ተሳትፎ ይደግፋል።
- ★ የልጆቻችን ትምህርት ጉዳይ የጋራ ኃላፊነታችን መሆኑ እምነታችን ነው።
- ★ ወላጆች ተሳትፎ ሲያደርጉ፣ ተማሪዎች ይበልጥ ውጤታማ እንደሚሆኑ እናምናለን።
- ★ የትምህርት ሥርአቱ እና በተናጠል ትምህርት ቤቶች፣ የቤተሰብ ተሳትፎን የሚደግፍ የጋራ መተማመንን እና መከባበርን ድባብ የመፍጠር ፕሮግራሞች እና ተግባሮችን የመዘርጋት ቁርጠኝነት አላቸው።
- ★ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የ "Title I" ትምህርት ቤቶች ሁሉም ሠራተኞች ስለ ወላጅ ተሳትፎ ያላቸውን ቁርጠኝነት ማስተጋባት እንዳለባቸው ይጠበቃል።
- ★ በትምህርት ቤት ሥርአት በሚገኙት ዋና ዋና ቋንቋዎች ለወላጆች መረጃ ይሰጣል።
- ★ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች እና የአካል ስንክልና ያላቸው ልጆች ወላጆች በተሳትፎ ጥረቱ ይካተታሉ።
- ★ ይህ እቅድ በጋራ ከወላጆች ጋር የዳበረ ሲሆን ከቦርድ ፖሊሲ "Board of Education Policy ABC"፣
- ★ የወላጅ እና የቤተሰብ ተሳትፎ/Parent and Family Involvementእና ከ MCPS ስትራቴጂክ ፕላን ጋር እንዲጣጣም ተደርጓል ።
- ★ በዚህ እቅድ፣ 'parent' የልጆች ትምህርት ቤትን ሱፐርቫይዘር በማድረግ የሚሳተፉ ወላጆችን፣ ሞግዚቶችን፣ እና ሌሎች የቤተሰብ አባላት እንደሚያሳትፍ ታሳቢ ያደርጋል።

### የእኛ አሠራር

- ★ የታይትል I የዲስትሪክት ደረጃ ወላጅ እና ቤተሰብ ተሳትፎ እቅድ ከታይትል I ሠራተኞች እና ታይትል I ከሚማሩ ተማሪዎች ወላጆች ከተዉጣጣ፣ ከታይትል I ወላጅ አማካሪ ኮሚቴ (PAC) ጋር በቅንጅት የተዘጋጀ ነው።
- ★ የታይትል I መስፈርቶች በዲስትሪክት ደረጃ እንዴት እንደሚተገበሩ እቅዱ መረጃ ይሰጣል።
- ★ የወላጆች አውደጥናቶች፣ የወላጆች ስብሰባ እና ሌሎች ኩነቶች ቤተሰቦች የግምገማ መሣሪያዎችን-መተግበሪያዎችን በመጠቀም ግብረ መልስ መስጠት የሚችሉባቸው አጋጣሚዎች ናቸው።
- ★ በግምገማ የተገኘው ግብረመልስ በየዓመቱ በስፕሪንግ ወቅት (PAC) ስብሰባ ላይ በዝርዝር ይተነትናል። ዕቅዱን ለማሻሻልና ወላጅን የበለጠ ለማሳተፍ የሚያስችሉ እድሎችን ለመፍጠር የሚረዱ ሐሳቦች ይሰጣሉ።
- ★ በእያንዳንዱ ታይትል I ት/ቤት የትምህርት ቤት እና የቤተሰብ ተሳትፎ እቅድ ወይም ንድፍ በማዘጋጀት ተመሳሳይ መስፈርቶችን ያካተተ የትምህርት ተሳትፎ ደረጃን ለመፍጠር ይውላል።
- ★ ትምህርት ቤቶች እያንዳንዳቸው በየዓመቱ በሚያካሄዱት የታይትል I የወላጅ ተሳትፎ ኮሚቴ እና የአመራር ስብሰባዎች ላይ የራሳቸውን የታይትል I የወላጅ እና የቤተሰብ የተሳትፎ እቅድ ደረጃ በመገምገም፣ በዝርዝር ከተመለከቱ በኋላ ክለሳ ያደርጋሉ።
- ★ የትምህርት ቤት ደረጃ ዕቅዱ በእያንዳንዱ ፎል ወቅት በጋዜጣዎች፣ በኤሌክትሮኒክ መገናኛዎች፣ እና በቤተሰብ ስብሰባዎች/አውደ ጥናቶች ጨምሮ በተለያዩ በርካታ መንገዶች ይሰራጫሉ።

# የ MCPS Title I ቤተሰቦችን በመደገፍ አቅም በመገንባት ያምናል ይኼውም፡- በስልጠና እና ሙያዊ ትምህርት በመስጠት ነው

## በወላጅ አክቲቪቲዎች የአቅም ግንባታ ይሰጣል

**ፓረንት አካደሚ**/Parent Academy፡- የ MCPS ፓረንት አካዳሚ በትምህርት ዓመቱ ውስጥ እንደሚከተሉት ባሉ የተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ፣ በተለያዩ ጊዜያት እና በተለያዩ ቦታዎች፣ በወር ቢያንስ ሁለት ጊዜ አውደጥናቶችን ይሰጣል፦

- ★ ስለ ስቴቱ አካዳሚያዊ የጥራት ደረጃዎችን መረዳት፣ ስለ ስቴት እና የአካባቢ አካዳሚያዊ ምዘናዎች፣ እና የልጅን ግስጋሴ እንዴት መቆጣጠር እንደሚቻል፥
- ★ የልጃቸውን አካላዊ፣ ማህበራዊ እና ስነ ልቦናዊ ደህንነት እንዲያድግ መደገፍ፤
- ★ የተማሪዎችን ስኬታማነት ለማሻሻል ከትምህርት ባለሙያዎች ጋር መሥራት እንዲሁም ወላጆች ከልጆቻቸው ጋር እንዲሠሩ መርዳት።

**የወላጅ አውደጥናቶች፡-** የታይትል I የትምህርት ባለሙያዎች ለወላጆች እና ለትምህርት ቤት ባልደረቦች በእያንዳንዱ ት/ቤት ማቴሪያሎችን እና ስልጠና ይሰጣሉ፦

- ★ የታይትል I መስፈርቶችን መረዳት
- ★ በቤትና በትምህርት ቤት መካከል የሐሳብ ልውውጥ ማድረግና የልምድ ልውውጥን ማዳበር
- ★ በቤት ውስጥ የልጆቻቸውን እድገት መደገፍ

**የትምህርት ቤት እና የቤተሰብ ተሳትፎ ሂደቶች፡-** የታይትል I የትምህርት ባለሙያዎች ትምህርት ቤትን እና ወላጆችን የሚደግፉት በ፦

- ★ በወላጆችና በት/ቤቶች በምርጥ ተሞክሮዎች ዙርያ የተሳካ የመማር ማስተማር ጥናቶችን ለማካሄድ በሚቻልባቸው ጥሩ ልምዶች ላይ በታይትል I ትምህርት ቤቶች ለሚያስተምሩ አስተማሪዎች መገልገያ ሪሶርሶችን እና ስልጠና መስጠት
- ★ ስኬታማ በሆነ የወላጅ-አስተማሪ ኮንፈረንስ ላይ ለመሳተፍ እንዲችሉ ለቤተሰቦች መገልገያዎችን-ሪሶርሶችን መስጠት
- ★ ወላጆች ስለተሞክሮአቸው ግብአት እንዲሰጡ እና ለቤተሰብ ተሳትፎ የተመደቡ ባጀቶች እንዴት ወጪ እንደሚደረጉ ውሳኔዎችን መስጠት የሚችሉበትን እድል ለመስጠት በየሩብ ዓመቱ በሚያደርጉ ስብሰባዎቻቸው ከቤተሰብ ተሳትፎ ኮሚቴ ጋር አብሮ መሥራት

## በሠራተኞች ስልጠና አማካይነት የአቅም ግንባታ

**የሠራተኞች ስልጠና፡-** በዋናው ጽ/ቤት ሠራተኞችና በትምህርት ቤት የሚሠሩ ሠራተኞች በመሆናቸው ቴክኒካዊ እገዛ የሚሰጣቸው በታይትል I ባለሙያዎች አማካኝነት ዓመቱን ሙሉ በተለያዩ መድረኮችና ከሥራዎቻቸው ጋር በሚገናኙ በተለያዩ ርእሶች ነው። ለትምህርት ቤቶች የሚሰጡት አንዳንድ ድጋፎች የሚያካትቱት፦

- ★ በትምህርት ቤትና በወላጆች መካከል ሰፊ ቦታ የሚሰጠው እና በትምህርት ቤት ደረጃ የሚከናወን የቤተሰብ እና የወላጆች ተሳትፎ እቅድ ማዘጋጀት
- ★ የትምህርት ቤት የሥራ ባልደረቦች ከወላጆች ጋር እኩል በአጋርነት እንዲሠሩ የሙያ ማበልጸጊያ እቅድ ማዘጋጀት እና ማዳበር
- ★ የልጆቻቸውን ትምህርት በሚመለከት ከቤተሰቦች ጋር በእኩል አጋርነት መገናኘት እና መተባበር
- ★ በትምህርት ቤት ደረጃ ለወላጅና ማህበረሰብ አስተባባሪዎች በወላጅ ተሳትፎ ባለሙያ-ስፔሻሊስት አማካይነት ስልጠና መስጠት።
- ★ የወላጅ እና የቤተሰብ ተሳትፎን ለማስፋት በትምህርት ቤት ደረጃ ወላጅና-ማህበረሰብ አስተባባሪዎችን ከሪሶርሶች እና ማህበረሰብን መሠረት አድርገው የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች ጋር ማገናኘት።

**የትምህርት ስፔሻሊስት ሥልጠና፡-** የታይትል I የማስተማር ሙያ ስፔሻሊስቶች በተግባራዊ አፈጻጸም፣ በማስተባበር፣ የፌደራል እና የስቴት መስፈርቶችን በማስፈጸም ረገድ እገዛ ያደርጋሉ። የታይትል I የሥራ ባልደረቦችም እንደዚሁ ከትምህርት ቤት የሥራ ባልደረቦች እና ከቤተሰቦች ጋር በሚጋሯቸው ጠቃሚ ጉዳዮች ዙርያ ስልጠና የሚያገኙ ሲሆን ይኼውም፦

- ★ የወላጅ እና የቤተሰብ ተሳትፎን በሚመለከት ማስረጃን መሠረት ያደረጉ ስትራቴጂዎች
- ★ ዝግጅት፣ ስልጠና፣ እና የቤተሰብ ተሳትፎ ባጀቶችን መቆጣጠር
- ★ በቤተሰብ ተሳትፎ የባጀት ውሳኔዎች ላይ ወላጆችን ስለማሳተፍ
- ★ ከፌደራል ስለሚሰጡ ገንዘቦች ተገቢ አጠቃቀም

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ትምህርት ቤቶችን መርዳት ቤተሰቦችን መርዳት መሆኑን ያምናል

## ትምህርት ቤቶችን መርዳት

የህጻናት ክፍል፣ Title I፣ እና የማገገሚያ ፈንድ (DECTRF) የወላጅ ተሳትፎ ስልቶችን ከ MCPS ቢሮዎች ጋር ያስተባብራል እና ያቀናጃል። ይኼውም፦

- ★ ዓመቱን በሙሉ በተለያዩ ኮሚቴዎች በንቃት በመሳተፍ ይከናወናል።
- ★ ለታይትል I ወላጆችን የመድረስ (outreach) እና የስልጠና ድጋፍ ጥረት ከተማሪ እና የቤተሰብ ድጋፍና ተሳትፎ ጽ/ቤት - Office of Student and Family Support and Engagement (OSFSE) እና ከወላጅና ማህበረሰብ አስተባባሪዎች ጋር ስብሰባ ማድረግ/መገናኘት።
- ★ ለታይትል I ወላጆች የወላጅ ተሳትፎን ለማረጋገጥ ቅድመ ምዋእለ ህፃናት/ሄድስታርት ጋር በመተባበር የስልጠና ጥረቶችን በማስተባበር የአሠራር ስርዓትን ማሻሻል።

## ትምህርት ቤቶችን ማስተባበር

ለታይትል 1 ትምህርት ቤቶች የ Title 1 የወላጅ እና የቤተሰብ ተሳትፎ ጥረቶች ቅንጅት እና የቴክኒክ ድጋፍ ከ DECTRF በ Title I የትምህርት ስፔሻሊስቶች አማካይነት ይሰጣል። ታይትል I የማስተማር ባለሙያ ስፔሻሊስቶች የሚሰጡት፦

- ★ የተማሪን ስኬት እና የትምህርት ቤትን አሠራር ለማሻሻል ለትምህርት ቤት የሥራ ባልደረቦች የሚሰጥ ድጋፍ፣ መመሪያ፣ እና እርዳታ ውጤታማ የሆነ የወላጅ ተሳትፎ እንቅስቃሴዎችን-አክቲቪቲዎችን ማቀድ እና ተግባራዊ ማድረግ።
- ★ በትምህርት ቤት/በወላጅ መካከል ጥምረት/ትብብር እድገት፣ በትምህርት ቤት ደረጃ የእቅድ ዝግጅት፣ እና ሌላም በወላጅ ተሳትፎ እንቅስቃሴዎች መደገፍ።
- ★ Title I የፌዴራል እና የስቴት መስፈርቶችን የሚደግፉ ሠነዶች በ DECTRF ውስጥ ይገኛሉ።

## የሚጠበቅ ስምምነት (ኮምፓክት)

የትምህርት ቤት/የወላጅ የተጠበቀ ስምምነት (ኮምፓክት) ግቦችን፣ የሚጠበቁ ውጤቶችን እና በጋራ የሚከናወኑ ኃላፊነቶችን ይገልጻል። ከቤተሰቦች ጋር በመተባበር፣ እያንዳንዱ ትምህርት ቤት ፎል ላይ ስምምነት (ኮምፓክት) ያዘጋጃል። ስምምነቶቹ (ኮምፓክቶች) በየዓመቱ ፎል ወቅት በወላጅና አስተማሪ ኮንፈረንስ ላይ እየተገመገመ ይፈረምበታል። የተማሪ ስኬታማነት ስምምነት (ኮምፓክት) በወላጅ እና በትምህርት ቤት መካከል የሚደረግ የጋራ ጥረት አካል ተደርጎ ይሠራበታል።

## ግብረመልስ-ምክረሃሳብ

ስለ ዲስትሪክታችን የወላጅ እና የቤተሰብ ተሳትፎ እቅዳችን ግብረመልስ እንቀበላለን።
እባክዎ ታይትል I የዲስትሪክት ደረጃ እቅድ ዳሰሳ ይሙሉ https://bit.ly/MCPSdistrict

Rocking Horse Road Center
4910 Macon Road, Room 204
Rockville 20852 ~240-740-4600